# የዓለም የሰላም ቀንን በማስመልከት የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ያስተላለፈችው የሰላም መልዕክት

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕገ ድንጋጌ የሆኑትን የወንጌል እሴቶችን የምታስፋፋው እነዚህ እሴቶች በሰው ልጅ ዘንድ ውስጣዊ ለውጥ እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ሰላምን፤ ደስታንና ስምምነትን ያመጣሉ በሚል ጽኑ እምነት ነው፡፡

የሰዎችን ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን ለመጠበቅ ለሰላምና ለልማት መሥራት ሁለተኛ እሳቦት መስጠት የሌለበት ጉዳይ እንደሆነ ቤተክርስቲያኗ በአጽንኦት ታምናለች፡፡ ለዚህም ነው ቤተክርስቲያኗ ከምትሰጣቸው ማህበራዊ አገልግሎቶች ባሻግር በሕ/ሰቡ መሃከል ሰላምንና አንድነትን ለማጠናከር በሀገር ደረጃ ባሏት 10 ሀገረስብከቶች አማካይነት ለሰላም ሥራ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የምትንቀሳቀሰው፡፡

በወዳጅነት እና ገንቢ የሆነ ልምድ እርስ በርስ በመካፈልና ልምድን በማጎልበት መንፈስ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተመሳሳይ የሰላም ተልዕኮ ካላቸው ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት ጋር ሰላምንና አንድነትን ለማጎልበት በጋራ ትሠራለች፡፡ ይህንንም የምታደርገው ለሰላም መስፋፋት የሚደረገው ጉዞ በተናጠል ለመወጣት አድካሚና አስቸጋሪ መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ለሰላም መስፋፋትና መጎልበት የሚደረገው እንቅስቃሴ የጋራ ጥረትን የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡ ይህም ከቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ መሠረታዊ መርሆ አንዱ የሆነውን የአንድነት /solidarity/ እሴትን ያስገነዝበናል፡፡ አንድነት /solidarity/ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚያስገነዝበን ከሌሎች ሰዎች ጋር በአንድነት በመሆን በጽኑ እምነትና ተጋድሎ ለሀገር እና ለመላው ዓለም የጋራ ጥቅም መሥራትን ነው፡፡

ሶስተኛውን ምዕተ ዓመት (ኢዩበልዩ) እንደጀመርን ራሳችንን ዝግጁ አድርገን ጊዜያችንን የምንቆጥበው ሰላምንና ልማትን ለማስመዝገብ ሀገሪቷ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ለመግታት ሳይሆን፤ ለዚሁ ለሰላምና ለልማት ለሚደረግ ጥረት እንደ እርሾ ሆነን በመሀከላችን አንድነት ተጠናክሮ ሰላማዊ ግንኙነት በብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ

እግዚአብሔር አገራችንንና ዓለማችንን እንዲባርካት፤ በአንድነት፤ በፍትህና በሰላም እንዲጠብቃት ይፀልዩም ዘንድ አደራ ትላለች።

**ሰላም በምድራችን ይሁን!**

**የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን**
**መስከረም 11 ቀን 2001**